# የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥና የአፈፃፀም ሥርዓት መመሪያ

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

*ሚያዝያ 2001 ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ*

# ***የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥና የአፈፃፀም ሥርዓት***

# ***መመሪያ ቁጥር 11/2001***

ተገቢውን የመንግስት ግብር ታክስና ቀረጥ ለመሰብሰብ እንዲቻል ግዴታ ያለባቸውን ግብር ከፋዮች ብዛታቸውንና የንግድ ሥራ ባህሪያቸውን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ግብር ከፋዮች በተገቢው መንገድ ግዴታቸውን መወጣታቸውን ለመከታተል እንዲቻልና በታክስ ሥርዓቱ ያልታቀፉ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ለይቶ የሕግ ማስፈፀም ተግባራትን ማከናወን አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 46 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥና የአፈፃፀም ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. <u>ትርጓሜ</u>

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፦

1) "የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር" ማለት ግብር በሚከፈልበት ንግድ ሥራ ወይም ገቢ በሚያስገኝ ማንኛውም ሥራ ላይ ለተሰማራ ሰው በባለሥልጣኑ የሚሰጥ አንድ የተለየ ቁጥር የያዘ የምስክር ወረቀት ነው፡፡
2) "የንግድ ፈቃድ" ማለት ለአንድ ንግድ ዘርፍ በፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን የሚሰጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማለት ነው፡፡
3) "የጣት አሻራ" ማለት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለመስጠት እንደ ብቸኛ መለያ የሚያገለግል እና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ተመዝግቦ የሚያዝ የአንድ ሰው የጣት ውስጣዊ ፈለግ ጭረት (finger print) ነው፡፡

4) “ሰው” ማለት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 የተጠቀሰውን ትርጉም ይይዛል፡፡
5) “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሆን የክልል መንግስታትና የከተማ አስተዳደር ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶችን ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማውጣት በሚገባው ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማውጣት ስለሚገባቸው

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመውሰድ ወይም የማውጣት ግዴታ ያለባቸው፡-

1) ግለሰብ ነጋዴ፣
2) ተቀጣሪ ሠራተኛ፣
3) ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሚያስገኝ የሙያ ሥራ የሚሠራ ሰው፣
4) መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣
5) በንግድ ሥራ የተሰማሩ የሃይማኖት ድርጅቶች፣
6) ኩባንያዎች፣ አክሲዮን ማኀበራት፣ የሽርክና ማኀበራት፣ የእሽሙር ማኀበራት /joint venture/ እንዲሁም በንግድ ሥራ የተሠማሩ ማናቸውም ማኀበራት ናቸው፡፡
7) የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች/ተማሪዎች

## 5. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ለማግኘት መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች

1) በግለሰብ ለሚካሄድ የንግድ ሥራ፣ በተቀጣሪና የሙያ ሥራ በሚሠራ ሰው፣
   ሀ/ የግብር ከፋዩ የከተማ ቀበሌ ወይም የቀበሌ ገበሬ ማኀበር መታወቂያ፣
   ለ/ የአመልካቹ /የግብር ከፋዩ/ ከስድስት ወር ወዲህ የተነሣው ፎቶግራፍ፣

ሐ/ አመልካቹ የቤተሰቡን ንግድ የወረሰ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሞግዚት ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋጋጥ ከፍ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ

ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2) ኩባንያዎች፣ አክሲዮን ማኅበራት፣ የሽርክና ማኅበራት፣ የእሽሙር ማኅበራት /joint venture/ እንዲሁም በንግድ ሥራ የተሠማሩ ማናቸውም ማኅበራት፣

ሀ/ የማኅበር መመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ፣

ለ/ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከስድስት ወር ወዲህ የተነሣው ፎቶግራፍና በግሉ ያወጣውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

ሐ/ አመልካቹ ወኪል ከሆነ ስለውክልናው የተሰጠውን ሕጋዊ ማስረጃ፣

መ/ ከማኅበርተኞቹ መካከል የውጭ አገር ዜጋ ካለ ማንነቱን የሚገልጽ ፓስፖርት ኦሪጅናልና ፎቶኮፒ እንዲሁም ከኢንቨስትመንት ጽ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ፣

ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3) የመንግስት የልማት ድርጅቶች፡-

ሀ/ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣

ለ/ ድርጅቱ የተቋቋመበትን ደንብ፣

ሐ/ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ምደባ ደብዳቤ፣

መ/ የሥራ አስኪያጁ የቀበሌ መታወቂያና ከስድስት ወር ወዲህ የተነሣው ፎቶግራፍና በግሉ ያወጣውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

ሠ/ የንግድ ፈቃድ ፎቶኮፒ፣

ረ/ አመልካቹ ወኪል ከሆነ ስለውክልናው የተሰጠውን ሕጋዊ ማስረጃ፣

ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

4) የመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች

ሀ/ የማቋቋሚያ አዋጅ ወይም ደንብ፣

ለ/ መስሪያ ቤቱ የሚወክለው ሰው የውክልና ደብዳቤና የግለሰቡ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

5) መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

ሀ/ የፍትሕ ሚኒስቴር የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣

ለ/ የሥራ አስኪያጅ ምደባ ደብዳቤና የግሉን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

## 6. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ግዴታዎች

ማንኛውም ሰው፡-

1) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለማግኘት በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብና የጣት አሻራ የመስጠት፣
2) የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት ከባለሥልጣኑ በቅድሚያ የማግኘት፣
3) ግለሰቡ የተለያየ የንግድ ዘርፍ ወይም ቅርንጫፎች በተለያዩ ቦታዎች ቢኖሩትም አንድ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ብቻ የማውጣት፣

ግዴታ አለበት፡፡

## 7. የጣት አሻራ መስጠት የማይጠበቅባቸው ድርጅቶች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(1) የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት በተቋም ደረጃ ብቻ የጣት አሻራ መስጠት አይጠበቅባቸውም፡፡

1) የመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች፣
2) የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣
3) የንግድ ማኀበራት /የአክሲዮን ማኀበራት፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር፣ የእሽሙር ማኀበር፣ የሽርክና ማኀበራት...../
4) መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
5) የማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ወኪል ስለወከለው ሰው ወይም ድርጅት በመወከል፣ ራሱን ችሎ የንግድ ወኪል በመሆን ፈቃድ አውጥቶ የሚሠራ ካልሆነ በስተቀር፡፡

## 8. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ስላልወሰዱ ግብር ከፋዮች

1) የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸውና በማንኛውም የንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያልወሰዱ

ግብር ከፋዮች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት ለማግኘት የምዝገባ ቅጽ ሞልተው በአንቀጽ 5 የተመለከቱትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለባቸው፡፡

2) በአንቀጽ 7 ከተመለከቱት በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት ግብር ከፋዮች የጣት አሻራ በመስጠት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

## 9. የምዝገባ ቦታ

1) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) የሚሰጠው እንደ አግባብነቱ በፌዴራል ወይም በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ይሆናል፣
2) ማንኛውም ሰው በሚኖርበት ወይም የንግድ ሥራው በሚገኝበት አካባቢ ባለው የገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት በመቅረብ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፣
3) ማንኛውም ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ለማግኘት መመዝገብ ያለበት ዋና መስሪያ ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ባለው የገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ይሆናል፣
4) ግብር ከፋዩ በአንድ ወይም በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ላይ የተሰማራ፣ በተለያዩ ዞኖች ወይም ክልሎች ወይም የከተማ አስተዳድሮች ውስጥ የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ከሆነ የሁሉንም አድራሻ ማስመዝገብ ይኖርበታል፣
5) በአንድ ቦታ የተሰጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ምስክር ወረቀት ለፌዴራል እንዲሁም ለሁሉም ክልልና ከተማ አስተዳደር የሚያገለግል ይሆናል፡፡

## 10. የምዝገባ ለውጦችና ማሻሻያዎችን ስለማስታወቅ

1) ማንኛውም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው ሰው በመመስረቻ ምዝገባ ጊዜ የሰጣቸውን ዝርዝር መረጃዎች ማለትም የአድራሻ፣ የንግድ ሥራ ዘርፍ አደረጃጀት ወይም አዲስ ቅርንጫፍ የመክፈት፣ ሥራ አስኪያጅና የካፒታል ለውጥ እንዲሁም የባለአክሲዮን መለዋወጥ እና የመሳሰሉትን ለውጦች

የሚያደርግ ከሆነ ለውጡ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለተመዘገበበት ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2) የተደረገው ለውጥ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት ላይ ያሉትን መረጃዎች የሚያስለውጥ ከሆነ /ለምሳሌ አድራሻ እና የንግድ ዘርፍ/ የቀድመውን የምስክር ወረቀት ይመልሳል፤ በምትኩም ሌላ የምስክር ወረቀት ታትሞ ይሰጠዋል፡፡

## 11. ምትክ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት ስለማግኘት

1) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት በተለያየ ምክንያት ከጠፋና ግብር ከፋዩ ለፖሊስ ያሳወቀበትን ማስረጃ ካቀረበ፣ ወይም
2) የምስክር ወረቀቱ በተለያዩ ምክንያቶች ከተበላሸ ግብር ከፋዩ ሲያመለክት የተበላሸውን መልሶ

ሌላ ታትሞ ይሰጠዋል፡፡

## 12. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት ስለሚመለስበት ሁኔታ

በሚከተሉት ምክንያቶች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት ለባለሥልጣኑ ሊመለስ ይችላል፡፡

1) ግብር ከፋዩ በተለያየ ምክንያት ገቢ የሚያስገኘውን የንግድ ሥራ ወይም ገቢ የሚያስገኘውን ሥራ ሙሉ በሙሉ ማቆሙን ሲያመለክትና ይኸው በባለስልጣኑ ተመርምሮ ሲታወቅና ሌላ የሚከፈል ቀረጥና ታክስ እዳ እንደሌለበት ሲረጋገጥ፣
2) ግብር ከፋዩ የንግድ ስራውን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በተለያየ ምክንያት ሲያቆምና ይኸው በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ የንግድ ሥራውን እንደገና እስኪጀምር የምስክር ወረቀቱ በባለሥልጣኑ አደራ ሥር ሊቆይ ይችላል፡፡
3) ግብር ከፋዩ በሞት ወይም በአደጋና በተለያዩ ምክንያቶች የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን ሲያቆም፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ቢኖርም በግብር ከፋዩ መሞት ምክንያት የሥራው እንቅስቃሴ ካልቆመና ወራሽ ወይም ሞግዚት ተተክቶ

የሚሠራ ከሆነ ሕጋዊ ወራሽነቱን ወይም ሞግዚትነቱን እስኪያረጋግጥና ስም እስኪያዞር ድረስ ለ12 ወር ብቻ የምስክር ወረቀት ላይመለስ ይችላል፡፡

## 13. አስተዳደራዊ መቀጫና የወንጀል ቅጣት

በዚህ መመሪያ መሠረት ግዴታዎችን አለመፈፀም ማንኛውም ግብር ከፋይ ግዴታውን ሳይወጣ ሲቀር እንደሚቀጣ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 የተመለከቱትን አስተዳደራዊ መቀጫና የወንጀል ቅጣት ያስቀጣል፡፡

## 14. የተሻሩ መመሪያዎች

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥና አፈፃፀምን በተመለከተ ቀደም ሲል የወጡ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

## 15. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ____________ ቀን 2001 ዓ.ም.**

**መላኩ ፈንታ**
**የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**